# መጋረጃው ያልተነሳ ተውኔት፣ ያልተፈታ እንቆቅልሽ!
## ክፍል ሁለት

ከበልጅግ ዓሊ

ባለፈው ሳምንት ለንባብ ያቀረብኩትን "መጋረጃው ያልተነሳ ተውኔት፣ ያልተፈታ እንቆቅልሽ" ክፍል አንድ በሚመለከት በጣም ብዙ የኢሜል ድጋፎችን አግኝቻለሁ። በዚሁ አጋጣሚ ለጻፋችሁልኝ በሙሉ ምስጋናዬን አቀርባለሁ። የደረሱኝ ኢሜሎች ከሁሉም የሕብረተሰብ ክፍል በመሆኑ ደስታዬ እጥፍ ነው። ከደረሱኝ ኢሜሎች በሙሉ አንድ እናት በልጃቸው አጽፈው የላኩት በጣም አሳዛኝ ነበረ። እነሆ

ውድ በልጅግ

እኛ የሚናገርልን አጥተን ፍትሕ ሳናገኝ እስካሁን ለቆየን እናቶች የአንተ ጽሁፍ ተስፋ የሚሰጠን ሆኖ አግኝቸዋለሁ ። ለዚህም ፈጣሪ ያሰብከውን እንዲፈጽምልህ እለምናለሁ። ከምርቃቱ በኋላ ወያኔዎቹ ስልጣን የወጡ ጊዜ የማጋለጥ ብለው በጠሩት ስብሰባ ላይ ብገኝም ለወያኔዎቹ ምንም ማጋለጥ እንደማልፈልግ ነበር የነገርኳቸው። መቼም ከልጄ ሃገሬ ትበልጥብኛለች በማለትና ለእነዚህ ሃገር አጥፊዎች ምንም ድጋፍ አላደርግም ብዬ ነበር። ይህንንም ልል የቻልኩበት ምክንያት መቼም ደርግ ተመልሶ አይመጣም ብዬ በማሰብ ነበር። አሁን ግን ደርጎች ተሰባስበው በእነርሱ ብሶ መንግሥቱን የሚቃወሙትን እንከሳለን ማለታቸውን ስሰማ ከልቤ አዘንኩ። በዚህም ምክንያት ደርጎቹ በከሰሱበት ፍርድ ቤት ቀርቤ ስለ ልጄ አገዳደልና በእሱም የተነሳ የተሰቃዬ አባቱን ታሪክ ለመመስከር ፍቃደኛ ነኝ። ለእዚህ ጉዳይ እግዜር ካበቃኝ ምን አደርጋለሁ። ቢሆንማ ሁላችሁም ተሰብስባችሁ ይህንን ሰውዬ ዞር በል ብትሉት በተሻለ ነበር።

አድራሻና ስልክ ቁጥር

ይህንን ኢሜል ስንመለከተው ምን ያህል የፍትሕ ጥያቄ አስፈላጊ መሆኑን እንረዳለን። እኚህ አሮጊት ሃገራቸውን ከልጃቸው አስበልጠው ለወያኔ የምስክርነት ቃላቸውን አልሰጥም አሉ። የአሮጊቷ ቃል የታላቅነት ድርጊት ምልክት ነው። ከልቤ አመሰገንኳቸው።

ከዚህ ተውኔት መጋረጃ ጀርባ የሚገኙ የአረመኔው መንግሥቱ ደጋፊዎች እንደዚህ ዓይነቱን የፍትሕ ጥያቄ ወደ ፖለቲካ ለመለወጥ የሚደርጉትን ጥረት አላቆሙም። ጥያቄውን የኢሕአፓ ብቻ ለማድረግና ለፍትሕ ጥያቄ የሚነሱትን ለመከፋፈል የሚደርጉትን ትግል በተለያየ ድረ ገጾች አንብቤያለሁ። ሌላው ሁሉ ይቅርና በቀይ ሽብር ወቅት የተሠራው ግፍ በኢሕአፓ ላይ ብቻ እንዳልነበር እሰቲ አነስተኛ ማስረጃ ላቅርብ፡ -

ይህ የሆነው ከፍተኛ 22 ቀበሌ 07 በሚገኘው እስር ቤት ውስጥ እንደ ኢትዮጵያውያን አቆጣጠር በ1970 ዓ.ም. ነው።

. . . በርካታ የቀበሌ ሊቀመንበሮች በስብሰባው ተገኝተዋል። በአሁኑ ወቅት በዚያ ጊዜ ስብሰባው ላይ ከተገኙት አንዳንዶቹ በአውሮፓና በሰሜን አሜሪካ ውስጥ የተደላደለ ኑሮ እየኖሩ ይገኛሉ። እስከ እኩለ ሌሊት ድረስ ስብሰባ ካደረጉ በኋላ ተበታተኑ። ከዚያ ቀን በኋላ ጥበቃው ይበልጥ ተጠናከረ። አንድ ቀን ሌሊት ሁላችንም ተቀሰቀስን። እንቅልፍ ስላልወሰደን ቶሎ ተነስተን ተቀመጥን። በመጀመሪያ ደሳለኝና ውብሸት ተጠሩ። በመቀጠልም ጆሆቫዎቹ ተጠሩ፣ ከዛም ከበርቴው ሰውዬ። ሁላችንም ቀይ ሽብሩ ሊካሄድ መሆኑ ገባን። ይህንን ወቅት ከማንኛውም ጊዜ በበለጠ አስታውሰዋለሁ። በሁሉም ፊት ላይ የአየሁት የሞት ስዕል ከዓይኔ ሊጠፋ አይችልም።

ደሳለኝና ውብሸት ሁላችንንም በርቱ ብለውን ወጡ። ለቀረነው ጓዶቻቸው የማበረታቻ ቃላቸውን ሰጥተው ሞትን በጀግንነት ሊጋፈጧት እየተጣደፉ፣ የቁስለኞችን እግር እንዳይረግጡ እየተጠነቀቁ ሄዱ። ቀጥለው የተጠሩት ጆሆቫዎቹ ነበሩ ። መጽሐፍ ቅዱሳቸውን ይዘው ተነሱ። ወደ አባታቸው ቤት እንደሚሄዱ በፈገግታ የመጨረሻዋን እስትንፋሳቸውን ለመተንፈስ በቆራጥነት ገሰገሱ።
በመጨረሻ የተጠሩት ምንም ያልተጠበቁትና ከበርቴ ተብለው የታሰሩት ነበሩ። እግራቸው ከዳቸው፣ መጮኽ አቃታቸው፣ የልጆቻቸው ፊት መጥቶ ፊታቸው የተደቀነ ይመስል፣ የልጃቸውን ስም ጠርተው ጫማቸውን እንዲሰጣቸው ጠየቁት። ከጥቂት ሰከንዶች በኋላ ነበር ሁኔታው የገባቸው። በክፍሉ ውስጥ የነበርነውን

እስረኞች አንድ በአንድ ከተመለከቱ በኋላ ልጆቼን ለማን ጥዬ ልሂድ? ብለው በመማፀን  ጠይቀው መልሱን ከትንሳኤና ከከሰተ የሚያገኙት ይመስል እየተጣደፉ ወጡ።

ከውጭ ድምፃቸው ይሰማናል። ሁላችንም ዓይናችን በእንባ ተሞላ፣ በዝምታ ተሰናበትናቸው። ወደ ውጭ አውጥተው እጆቻቸውን አሰሯቸው። አሁንም ይጮሃሉ።
"ኧረ ልጆቼን ለማን ጥዬ?"ብለው ይጮኻሉ።
"ትንሳኤ ምን አደረግሁ?" . . . . .   ልጆቼ ማን አላቸው ? . . . . እባክሽ የዛሬን ተይኝ . . . . ሁለተኛ ያልሸኝን ሁሉ እሺ እላለሁ . . .  ንብረቴን ሁሉ ውረሱት . . .  ከባዶ እጀምራለሁ . . .  እግርሽ ላይ ወድቄ ልለምንሽ . . .  ልጆች የሉሽም? . . .  ከሰተ እስቲ አንተ ተለመነኝ፤  . . . ከነገ ዛሬ ትፈቱኛላችሁ ብዬ ስጠብቅ ?. . . .፣ ኧረ ባካችሁ በልደታ ! . . .  ኧረ ባካችሁ በልጆቻችሁ . . .  ስለ ወንድ ልጅ አምላክ ! . . . . ግረፉኝና ሃብቴንም  ሁሉ ወስዳችሁ ተውኝ . . . . . "መሪር የሲቃ ጮኸት ደግሞ በመሃል ያሰማሉ . . . ፣ "ትንሳኤ ሴት አደለሽም ? . . . ልጆች የሚሸከመው ማሕፀንሽ አይለመንም ? . . .  " ወደ ሌሎቹ የከበቡዋቸውን አብዮት ጥበቃዎች እየተማጠኑ    "እባካችሁ እስቲ እናንተ ለምኑልኝ . . .   ሽማግሌ  ሁኑኝ . . .  ለልጆቼ እንጂ ለእኔ ሞትም፣ ድኅነትም ፣ መከራም፣ ስቃይም አዲስ አደይለም    . . .  ጎበዝ ! . . .  የሃገር ወንድ ሁሉ ስሙኝ እንጂ ! . . .  አልገደልኩ . . .  ደም አልተቃባሁ . . . . . ለምን ይኸ ሁሉ?  . . . " ለጥያቄያቸው መልስ ሲያጡ ደግሞ . . . .  "ኧረ ባካችሁ አንድ በሉ . . .   ጨነቀኝ እኮ ዝም አትበሉ . . . ዝምታው ምንድነው . . . . "
ከትንሽ ጊዜ በኋላ የትንሳኤ ድምፅ  አንባሮቆ ልመናቸውን ገታው ።

" ዝም በል አትለፍልፍ . . . አብዮቱ አንተን የመሰለ አድኃሪ አይፈልግም  አይፈልግህም. . . "   የሚያሰቅቅ የፌዝ ሳቋን በቀጭኑ ለቀቀችው።"  ትሞታለህ ! . . . . " አለች ደጋግማ ።
ድምፃቸው  ተስፋ ባጣ ሁኔታ ተሰበረ።   እሺ እንግዲህ"ልጆቼን ለማንም አደራ አልልም . . .  ላንቺ ነው አደራ የምልሽ . . .  ማንም የለኝም አደራ የምለው . . . .በምድር የሰጠሁሽን በሰማይ እቀበልሻለሁ . . .  የሴትነት ማሕፀንሽ  በልጆች አልለመንም ካለ . . . ካለ ጥፋቴ ልትገይኝ ከፈለገሽ . . .  የልጆቼን አደራ አንቺው ተቀበይኝ . . .  እንደ ልጆችሽ አርገሽ አሳድጊልኝ . . .  እንዳይርባቸው ፣ እንዳይጠማቸው አደራ   . . .   "።  ድምፃቸው እየራቀ እየራቀ ሄደ። ከግቢው መኪናዎች ተከታትለው ሲወጡ ይሰማናል። ጥቂት ቆይቶ ከርቀት የጥይት እሩምታ ሲወርድ ሰማን ። በሩቅ።

በኋላ እንደሰማነው   ብሪሞ ገደል ከዳገቱ ላይ አቁመው ወደ ገደሉ በጥይት እየመቱ ከተቷቸው። ማንም ሬሳውን እንዳያነሳው አብዮት ጥበቃዎች ሲጠብቁ ዋሉ።  አስከሬኖቹ ከሰዓት በኋላ ተነሱ። ብሪሞ በደም የራሰ ምድር ሆነ።
ከብዙ ዓመታት በኋላ የጆሆቫዎቹን ፎቶ አገኘሁት ።


Faces we expect to see in the resurrection. All were murdered for their loyalty to the good news. From top left: Ayele Zelelew, Hailu Yemiru, Wubie Ayele, Kaba Ayana, Gebreyohanes Adhanom, Adera Teshome, Wondimu Demera, Kasa Gebremedhin, Eshetu Mindu

ከፎቶግራፉ ውስጥ ሦስቱ ከነበርኩበት ሶደሬ ክፍል ተወስደው የተገደሉ ናቸው።  ብሪሞ ገደል ውስጥ ተገድለው የተጣሉ። ሌሎቹም ከሌላ ቦታ ተይዘው የተገደሉ የሃይማኖቱ ተከታዮች ነበሩ።

የፍትሕ ጥያቄው የተወሰነ ክፍል ብቻ አለመሆኑን ለማሳየት ከላይ በፎቶግራፍ የተደገፈ መረጃዬን አቅርቤለሁ። እነዚህ የጆሆቫ እምነት ተከታዮች ከተገደሉበት ምክንያት አንዱ የሲ. አይ. ኤ ቅጥረኞች ተብለውና ኢሕአፓ ይውደም የሚለውን መፈክር ባለማለታቸው ነበር።ዛሬ ለእንደ እነዚህ ዓይነቶቹ በግፍ ለተገደሉ ዜኞች ፍትሕ መጠየቅ ለዴሞክራሲ የሚታገሉ ወገኖች ሁሉ ተግባር መሆን አለበት።

ከዚህ በላይ በጣም ብዙ መረጃ ማቅረብ ይቻላል። ደርግ በግፍ የገደላቸውን በሚመለከት ከእኔ በላይ ብዙ የሚያውቁ እንዳሉ አልጠራጠርም።  ስለ እነ ጄኔራል ፈንታ በላይ እና ሌሎቹም በግፍ የተገደሉ ጄኔራሎች ብዙ የምታውቁ ስላላችሁ ለፍትሕ ምስክርነታችሁን ለእናንተ እተዋለሁ። በኃይማኖትም በኩል እንደዚሁ። በተለይ በግፍ ለተገደሉት ጳጳስ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስትያን ድምጿን ካላሰማች ይገርመኛል።

ሁላችንም በዛ የግፍ አገዛዝ ግፍ የደረሰብን የፍትሕ ጥያቄያችን መቆም የለበትም። የአረመኔው ደጋፊዎች በልዩ ልዩ መንገድ ተቃዉሟችንን እንዳናሰማ ጫና እያደረጉ ነው። ከዚህም አንዱ ጥያቄውን ወደ ፖለቲካ ክርክር ለመለወጥ የሚደረገው ጥረት ነው። አረመኔውን መንግሥቱን እንደ ሃገር ወዳድ ፣ ተገድዶ እንደ ተሰደደ ለማስመሰል ብዙ የፈጠራ ተውኔቶች እያየን ነው። ከተውኔቱ መጋረጃ ጀርባ እንቆቅልሽ ያዘለ ምሥጢር አለ።

በዚህ የአረመኔው መጽሐፍ ተውኔት ጀርባ ያሉ ጋዜጠኞች "ቂም ቋጥሮ መነሳትና አሳታሚውን ለጉዳት መዳረግስ ይገባል?" ብለው ይጠይቃሉ። የፍትሕ ጥያቄ የቂም በቀል ወይም የወዳጅ ነጋዴ ትርፍ ጉዳይ አይመስለኝም። የሰብዓዊ መብት ጥያቄ የፍትሕ እንጂ ለአንባቢ እንተወው የሚባል የሥነ ጽሁፍ ውድድርም አይደለም። ለዚያች ለተበደለች እናት፣ ለዚያ ለተጎዳ አባት ማን በጥሩ አማርኛ መጽሐፍ ጽፎ፣ ማን አርሞለት፤ማን በድረ ገጽ ችሎት ላይ  ፍርድ ሊሰጥ ነው?

አሁን እንደምንመለከተው ወንጀለኛው ወንጃይ ሆኖ ከተውኔቱ ጀርባ በተሰበሰቡ ደጋፊዎቹ እውነት እየተዛባ አይደለም እንዴ ? "ዓይን ያጠፋ፡ ዓይኑ ይጥፋ"  የሚለው ተረት አለ ቦታው የተሞነጀረ ይመስለኛል። ካለ ፍትሕ ሲገድል የነበረን መሪ ከመጽሐፍ ገቢ አያትርፍ ብለው የጠየቁትን "ዓይን ያጠፋ ዓይኑ ይጥፋ ብለዋል" ተብሎ ከተተረጎመ ሲያርሙት የከረሙት መጽሐፍም ከዚሁ የማይሻል ፍርደ ገምድል  ነው ማለት ነው። ጎበዝ የፊት ታሪካችንን መለስ ብለን ማየት ይኖርብናል። የሠርቶ አደር ጋዜጣን አንገዛም ብለው የታሰሩ እንደነበሩ ልንዘነጋው አይገባም። ማን ደግሞ ሠርቶ አደርና አዲስ ዘመን ላይ የመፃፍ ባለ ሙሉ መብትና አምደኛ እንደ ነበረ መረጃ ማቅረብ ይቻለል። ለእኔ የደላኝን ሥርዓት አትውቀሱ ካልተባለ በስተቀር በፕሮፖጋንዳ  ስለ አገለገልነው ፋሽሽት መንግሥት በግል ለሠራነው ጥፋት ይቅርታ መች ጠይቀናልና ነው።

ለነገሩ ብዙዎቹ ሲጽፉ በቀይ ሽብር የተገደሉትን እያዳነቁ ሲጽፉ ተመልክቻለሁ። ታዲያ እንደዛ ለሚያደንቋቸው ወጣቶች ለምን ፍትሕ አይጠይቁላቸውም? በተንኮል የተሞላው የማላገጫ ብዕራቸው ለተሰውት ሰማዕታት ያላቸውን  ሃዘን አያሳይም ። ለእኔ ይህ ቀልዳቸው "ጥሩ ኢሕአፓ የሞተ ኢሕአፓ ብቻ ነው " የሚል  ማላገጫ ይመስለኛል።

የፋሽሽቱን መጽሐፍ ተቃዋሚዎች ያደረጉትን እንቅስቃሴ አሳታሚውን ለመጉዳት የተደረገ ለማስመሰል የሚደረገው ርብርቦሽ አሳዛኝ ነው። እዚህ ላይ አሳታሚው አምባገነኑ በሠራው ትራጀዲ ላትርፍ እስካላለ ድረስ ተቃውሞው አይመለከተውም። የሰብዓዊ መብት ታጋዮች የሚታገሉበትን ዓላማ ከግለሰብ ትርፍ አንፃር መመልከት ከጀመሩ ፍትሕን ማዛባት ነው የሚሆንባቸው። ወንጀለኛውን ካለፍርድ እስካልገደሉት ድረስ ከሚያገኘው ማንኛውም ጥቅም ቢያግዱት ምኑ ላይ ነው ስህተቱ ?

ይህ በጣም የሚገርም ነው። ተዋንያኖቹ መንግሥቱን በቀጥታ መደገፍ ስላልቻሉ በእመጫትነት አሳታሚውን ይዘው ብቅ ያሉ ይመስለኛል። በምሳሌ ለማስረዳት ልሞክር። ከአምባገነን መሪዎች ጋር ለትርፍ የሚሠሩ ጓደኞቻችንን ለመርዳት ሲባል ከአሁን በኋላ የሚተላለፉ የተቃውሞ ሰልፍ ጥሪዎች እንዲህ መሆን አለባቸው ማለት ነው?

> "የወያኔው ፋሽሽት መሪ መለስ ወደ ዋሽንግተን ዲሲ አባሎቹን ሊያነጋገር  በሚቀጥለው ወር ሊመጣ ነው የሚል ዜና አለ። ይህንን በሚመለከት የተቃውሞ ሰልፍ ልናዘጋጅ አስበናል። በዚህ ወቅት ለትርፍ ሲባል የተዘጋጀ ዝግጅት ካለ ቀድማችሁ አሳውቁንና ተቃውሟችንን እናቆማለን። አንድ ኢትዮጵያዊ ነጋዴ ከመጉዳት ይልቅ የወያኔው መሪ ካለተቃውሞ የፈለገውን አድርጎ መሄዱ የሚሻል መሆኑን ስለምናምን ከአምባገኑኑ ጋር ቢዝነስ የምትሠሩ በሞላ ቀድማችሁ ታስታውቁን ዘንድ እንጠይቃለን። ይህ ሳይሆን ቀርቶ ለሚደርስባችሁ ኪሳራ ተጠያቂ አንሆንም።  የነፃው ገበያ ጠላቶች ብትሉንም የምንቀበል መሆናችንን ከወዲሁ እናሳውቃለን።"

ይህ ቀልድ ነው ብላችሁ የምታስቡ ካላችሁ ተሳስታችኃል። ከአሁን ወዲህ ማናቸውም ተቃውሞ ከመደረጉ በፊት እንደዚህ ዓይነት ማስታወቂያ ማውጣት አስፈላጊ ነው። የመንግሥቱን መጽሐፍ መቃወምን በሚመለከት እንደዚህ ዓይነት ማስታወቂያ ባለመደረጉ "የነፃው ፕሬስ ጠላቶች" የሚል ጽሁፍ በድረ ገጾች ያነበብን ከዚህ የተለየ ሰሜት አላደረብንም። መንግሥቱ በግፉ ማትረፍ የለበትም፣ ለፍትሕ መቅረብ ነው ያለበት ብሎ መጠየቅ የፕሬስ ጠላቶች ማስባሉ ጸሐፊዎቹ ምን ያህል ለጓደኛቸው እንደቆሙ ያሳይ እንደሆን እንጂ ሌላ የሚያመጣው  ለውጥ የለም። ከተውኔቱ ጀርባ የሚገኙት ጋዜጠኛ የሚሉን ይህንኑ ነው። "እኛ የምንደግፈውን አትቃወሙ። ከተቃወማችሁን ደግሞ ነፃው ፕሬስ በእጃችን ነውና እንወጋችኋለን።" . . . አሳፋሪ ተግባር!። ስንት ጀግኖች የሞቱለተን፣ የተሰቃዩለትንና አሁንም በመሰቃየት ላይ ያሉበትን የነፃ ፕሬስ ትግል ለግል ወዳጅ መጠቀሚያ ማድረግ።

ከተውኔቱ መጋረጃ ጀርባ ያላችሁ ግለሰቦች፣ ድረ ገፆች፣ ራዲዮኖች፣ ዶክተሮች፣ ፕሮፌሰሮች  የጓደኞቻችሁን፣ ወዳጆቻችሁን፣ ሌሎች መነካት የለባቸውም  የምትሏቸዉንና ከዚህ የዴሞክራሲ ትግል ማትረፍ የሚፈቀድላቸውን ግለሰቦች የስም ዝርዝር ማሳወቅ ግዴታችሁ መሆኑን አትዘንጉ። አለበለዚያ አምባገነንን

ስንቃወም "የነጻው ፕሬስ ወዳጆችን" መጉዳት እንዳይሆንብን። የነፃው ፕሬስ ወዳጅነትና ጠላትነት በእናንተ የተንሻፈፈ ሚዛን ቢታይ ኖሮ በጣም ጥቂት ገንዘብ ያላቸው ብቻ ወዳጅ ሆነው ይቀሩ ነበር።

እዚህ ላይ ከተውኔቱ መጋረጃ ጀርባ የሚገኙ የሚሉን "አንድ የንግድ ሰው ከሚነዳና ቢዝነሱ ከሚከሽፍ አንዲት ደሃ አሮጊት "ድፍት" ብላ ያለ ፍትሕ ትቅር። ይች መናጢ ደሃ ልትጠቅመን ነው ?- በምን አድርጋ ልትጮኽብን ? በየትኛው ድረ ገጽ ልትሳደብ ? ዓይኖቿ በእንባ ይፍሰሱ። የልጇ ገዳይ ለፍርድ ሳይቀርብ ለዘላለም ይቅር። ለዚህ ለድሃ ሽማግሌ ምንም ማድረግ ለማይችለው ቤቱን ዘግቶ ያልቅስ እንጂ የምን ፍትሕ መጠየቅ። ዋናው ቁምነገር የዘመኑ ነጋዴ ኪስ መደለቡ ነው።"

ይህ ነው የዘመናችን የሰብዓዊ መብት ታጋዮች ፤ "የንፁሕ ኢትዮጵያዊነታቸው" ምልክቱ። ይህ ነው የእከክልኝ ልከክልህ የጥቅም ትግል መሠረቱ ፤ ይህ ነው የተውኔቱ አራሚዎች ድንፋታ።

እስቲ ይህንን በምሳሌ ላስረዳ፡ -

> መለስ ተገዶ ከሃገሩ ይሰደዳል እንበል ። እንደተለመደው መለስ ደግሞ መጽሐፍ ይጽፋል። ሁለተኛው አምባገነን የራሱን ታሪክ የጻፈ ተብሎ ይደነቃል። በመለስ ግፍ የተሠራባቸው ይቃወማሉ። አይ እዳቸው! አፈኑት ፤ እንዳያጋልጣቸው ፤ የነጻው ፕሬስ ጠላቶች። ንፁሁን ኢትዮጵያዊ ጎዱት። ሌላም ሌላም . . .

በመለስ ሲሆን ያስጠላል አይደል? መንግሥቱን ማሞገስ፣ የእሱን መጽሐፍ ማሳተም ወይም ለፍርድ አይቀርብም ብሎ መታገል እንደዚሁ ያንገፈግፋል። ለደጋፊዎቹ ይጣፍጣል እንጂ ለተጎዱት እንዲህ ነው የሚመረው።

መንግሥቱንና መለስን ማወዳደር የለብንም ። " መንግሥቱ ሃገሩን ይወዳል . . . ቆራጥ ነበር . . . ተገዶ ነው የጠፋው . . . " የሚል ምክንያት ትደረድሩ ይሆናል። ግን ይህ ሁሉ የመከራከሪያችሁ ነጥብ በፍትሕ አንፃር፣ በሕግ አንፃር የሚያመጣው ለውጥ የለም። ጥያቄው ደግሞ የፍትሕ ነው። ምንአልባት ይህ የመከራከሪያ ነጥባችሁ በሠራችሁት ግፍ የቆሰለውን ኅሊናችሁን ያሽላችሁ ይሆን እንደሆን እንጂ በዚያ ዘመን የተፈጸመዉንና ዓለም ያመነበትን ግፍ መጠን ለስንዝር እንዳችም አይቀንሰውም። እንዲያውም የግፍ ግፍ ሆኖ በተበዳዮቹ ቁስል ላይ ጨው እየጨመራችሁ በሥቃያቸው እንድትሳለቁ ይጠቅማችሁ እንደሆን እንጂ።

ምሳሌዬን ልቀጥል፡ -

መለስ በመጽሐፉ ምስጋና ብሎ ስብሐት ነጋንና በረከት ስምዖንን ቢጠቅስ። መለስ በመጽሐፉ ውስጥ ስለ 1997ዓ.ም. ምርጫ ሲጽፍ እንዲህ ቢል

> "ሰልፍ አትውጡ ብለን መከርናቸው። እንቢ አሉ። ታገስናቸው። ግን አላቆሙም ። የኢህአዴግ ስብሰባ ተደረገ ። ስብሰባው ሞቀ ። አንዱ ተነሳና ይገደሉ አለ። እኔ ምንም ማድረግ አልቻልኩም ። ተገደሉ ። በወቅቱ ሰላማዊ ፖሊሶችም ተገድለዋል።. . ."

የዛን ጊዜ ደግሞ የመለስ ደጋፊዎች እንደ አሁኑ የተውኔቱ ተካፋዮች ፡ -

> "መጽሐፉን በድረ ገጽ የለቀቁት ልክ ልካቸውን ስለነገራቸው ነው። አረጁ . . . ድርጅት ያረጃል እንዴ? . . . አልጠፉም እንዴ?. . . አሉ እንዴ? . . . ተው እየተባሉ ሰልፍ ስለወጡ ነው፣. . . ፖሊሶች ስለገደሉ ነው. . . ምን ያድርግ ሃገር ወዳድ ነበር። ሌላም ሌላም አሉባልታ . . .

እሲኪ አንድ ጊዜ መለስ ብላችሁ መንግሥቱን በመለስ ቦታ ቀይሩትና ሁኔታውን ተገንዘቡት። እውነቱን ግልጽ አድርጎ ያሳያችኋል። አምባገነን አምባገነን ነው። ፍትህ ደግሞ ለተበደሉ መሆን አለበት። ከሰሞኑ የመንግሥቱ ደጋፊዎች ጫጫታ የምናየው የፍትሕ አድልዎ ለንዋይ ሲባል በድረ ገጽ፣ በሚዲያ ሲንጸባረቅ ነው። መንግሥቱ ለፍርድ ይቅረብ ማለታቸውን ትተው፣ በሥነ ጽሁፍ ጥራት፣ በድረ ገጽ ርብርቦሽ እሱን ነፃ ለማውጣት ነው ርብርብ ሲያደርጉ ነዉ የሚታየው።

ሂትለር በሕይወት ቢኖር ለፍትሕ ሳይቀርብ መጽሐፍ እንዲጽፍ ይፈቀድለታል ብላችሁ ታምናላችሁ? ለመሆኑ የትኛዉ ነዉ መቅደም ያለበት፤ ፍትሕ ወይስ መጽሐፍ? መንግሥቱ ነፃ ነኝ ካለ ለምን ራሱን ለፍርድ አያቀርብም? ለምንስ መደበቅ አስፈለገው? ደጋፊዎቹ በመጽሐፍ ከሚደግፉት በሕግ ፊት ራሱን ነፃ አውጥቶ እነርሱን ከመሸማቀቅ፣ እሱም ከመደበቅ እንዲድን ጥሩ ጠበቃ ቢቀጥሩለት ይሻላል።

የፍትሕ ጥያቄ የአንድ አሳታሚ ድርጅት የባንክ ሂሳብ ጥያቄ አይደለም። በመንግሥቱ የተበደሉት ቢችሉ ይህንን አረመኔ ለፍርድ ቢያቀርቡት በወደዱ ነበር። ግን በዚህ ፍትሕ በጎደለበት ዓለም ሀገራችንን ለጥቅም ሸጦ፣ ከሕግም ፊት ተደብቆ ይኸው በመንደላቀቅ ይኖራል። አሁን ደግሞ ሌላዉ ቢቀር ይህ አረመኔ በግፉ እንዳያተርፍ በተቻላቸዉ መንገድ የታገሉትን ሊያሰድባቸው ባልተገባ ነበር። ከፍትሕ ይልቅ ጓደኛ ይበልጥብናል ያሉ ምሁራን ነን ባዮች በሃገራችን ላይ ታላቅ ግፍ የተሰራባቸውን ቤተሰቦች፣ እናቶችንና አባቶችን ልብ የሚሰብር ተግባር እየፈጸሙ መሆኑን ሊያዉቁት ይገባል። ሌላው ቢቀር አሳታሚውን ለመርዳት ከሚያደርጉት ጥረት ጋር ይህ አረመኔ ለፍርድ ይቅረብ ብለው ሲጠይቁ አይታዩም።

በጣም የሚያሳስበው ጉዳይ ከዚህ መጋረጃው ያልተነሳ ተውኔት ጀርባ እነማን ናቸው የሚገኙት? ከዚህ ተውኔት ጀርባ እነማን እንዳሉ ማወቅ ብዙ ከባድ አይደለም። ትንሽ መጋረጃውን መግለጥ ነው። የመንግሥቱን ምስጋናና ቀጣይ አንድ አራት ገጽ ማንበብ ነው። እነማን ከዚህ መጽሐፍ ጀርባ ተደርድረው ይገኛሉ ።


ምስጋና

አብዮታችን ከተቀለበሰና መንግሥታችን ከፈረሰበት ማግሥት ጀምሮ ታላቁን የኢትዮጵያ ሕዝብ አብዮት ታሪክ ይዘኸው እንዳትሞት በማለት ከማንም ቀድሞ የቀሰቀሰኝ የኢትዮጵያ ሠርቶ አደሮች ፓርቲ ማዕከላዊ ኮሚቴ አባል ጓድ ካሳ ከበደ!

በተመሳሳይ ከመቀስቀስና ከማበረታታት ባሻገር ለታሪኩ በማብራሪያነት የሚፈልጋቸውን የተለያዩ ሰነዶች፣ መረጃዎችና መጻሕፍት እያፈላለገና እያሰባሰበ ከሰሜን አሜሪካ እስከ ደቡባዊ አፍሪካ ድረስ በመላክ ርዳታ ያደረገልኝ፣ የኢትዮጵያ ሠርቶ አደሮች ፓርቲ ማዕከላዊ ኮሚቴ አባል ጓድ ፍስሀ ገዳ!

በጓድ ፍስሀ አማካኝነት ተመሳሳይ ርዳታ ያደረጉልኝና ነገር ግን በዚህ ቅፅ ለደህንነታቸው ስል ስማቸውን ያልገለፅኩት ሁለት ጓዶች!

በእጅ ጽሑፍ የተዘጋጀውን የታሪኩን ረቂቅ በኮምፒውተር የተየቡልኝን እህትማማች እህቶቼ ትዕግሥት እና ማህደር እየለ!

ለመጽሐፉ ዝግጅት የሚያስፈልጉኝን ቁሳቁሶች በማቅረብ ብቻ ሳይሆን የእኔንም ጤንነት በመንከባከብ፣ በመላላክ እንደኔው ፍላጎት ቢሆን ኖሮ ከወሰደብኝ ጊዜ ባጠረ ጽፌ እንድጨርስ ከእኔ ባለመለየትና በመትጋት የረዱኝ ውድ ባለቤቴ ጓድ ውብእንች ቢሻው፣ ልጆቼ ዶክተር ትምህርት፣ ዶክተር ትዕግሥትና ዶክተር አንድነት፣ እንዲሁም የልጅልጆ ወጣቷ ህሊና ለእኔ ብቻ ሳይሆን የታሪኩ ባለቤት ለሆነው የኢትዮጵያ ሕዝብ ባለ ውለታ ስለሆኑ ልባዊ ምስጋናዬን አቀርብላቸዋለሁ።

ኮ/ል መንግሥቱ ኃይለማርያም

መስከረም ወር 2004 ዓ.ም
ሐራሬ፣ ዝምባብዌ

ከዚህ አረመኔ የምሥጋና ጽሁፍ እንደምትረዱት የተውኔቱ መጋረጃ ሲገለጥ የሚወጡት እነ ማን መሆናቸውን ነዉ። ለመሆኑ ሁለቱ የተደበቁት እነ ማን ይሆኑ? ። መንግሥቱ አሁንም የኢሠፓ ማዕከላዊ ኮሚቴ እንዳልፈረሰ ነው የሚነግረን። ደባው ሁሉ በኢሠፓ ማዕከላዊ ኮሚቴ እንደተገመደ ነዉ የሚያስረዳን ። ለዚህም ነው ሁላችንም ነቃ ብለን መጠበቅ ያለብን፤ ውዳቂዉ ኢሠፓ በሌላ መልኩ ዳግም እንዳያቆጠቁጥ።

እያንዳንዱ አምባገነን በሥልጣን በነበረበት ጊዜ የፈለገውን ሲያስር፣ ሲገድል ቆይቶ ከሥልጣን ሲወገድ ደግሞ በመጽሐፍ ንግድ ምክንያት የፍትሕ ጥያቄ ተንጋዶ፣ አምባገነኑም ትርፉን እየዛቀ የሚኖርበት ዘመን ማክተም አለበት። ሥልጣን ላይ በነበረበት ወቅት ለሠራው ጥፋት በሕግ ፊት እንጂ በደጋፊዎቹ ጫጫታ በድሪ ገጽና በሜዲያ ፍርድ መሰጠት የለበትም የሚል ጽኑ እምነት አለኝ ። ይህ ከሆነ ብቻ ነው ገዥዎቻችን ተጠያቂነት እንዳለ የሚያውቁት። በሰሞኑ ግርግር ለመለስም ቢሆን ከሥልጣን በኋላ ያለዉ ሕይወቱ ተስፋ እንዲሰጠው እየተደረገ ነው። ለመንግሥቱ እየተደረገ ያለው እንክብካቤ ለመለስ ጫን ያለ የመጽሐፍ ሽያጭ ኮንትራት እንዲያስብ ያደርገው እንደሆን እንጂ ወደ ፍርድ ቤት የሚወስደዉ ወገን እንደሌለ ከልምድ ይማራልና ነው። ለምናደርገው የዴሞክራሲ ጥያቄ ሁለት መስፈሪያ እንዲኖረን አይገባም። አንድ ለምንወደው ሌላ ለምንጠላው።

ለፍትሕ የሚታገሉ ሁሉ በሰላም ይክረሙ !

Beljig.ali@gmail.com

ለንደን፣ ጥር 2004 (feb. 2012)

በልጅግ ዓሊ